በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የገቢዎች ሚኒስቴር
THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA
MINISTRY OF REVENUES

ቀን መስከረም 28 2012
Date
ቁጥር 1/164/12
Ref.No

**ለጉምሩክ ኮሚሽን**
**<u>አዲስ አበባ</u>**

ጉዳዩ፡- <u>መመሪያ ስለመላክ</u>

ዕቃ በዋስትና ስለሚለቀቅበት ሁኔታ ለመወሰን የወጣውን መመሪያ ቁጥር 166/2012 ከዚህ ጋር በማያያዝ የላክን ስለሆነ በመመሪያው መሠረት እንዲፈፀም አሳስባለሁ፡፡

ከሰላምታ ጋር

አደም አቤቤ
ሚኒስትር

<u>ግልባጭ፣</u>

- ለሕግ ተገዥነት ዘርፍ
  <u>ገቢዎች ሚኒስቴር</u>

Phone: +251 11 662 98 00/ 01/02/03/04/05/06/07/08 Fax: /+251 11 662 98 17
face book page: ministry of revenues. FBP: mor Ethiopia Twitter: erca@twitt
web site: http//www:erca.gov.et P.o. Box: 2559 Addis Ababa, Ethiopia

የበለፀገች ኢትዮጵያ!

# ዕቃ በዋስትና ስለሚለቀቅበት ሁኔታ ለመወሰን የወጣ

# መመሪያ ቁጥር 166/2012

**ገቢዎች ሚኒስቴር**

መስከረም 2012 ዓ.ም

በኢ.ትዮ.ጵያ ገቢዎች ሚኒስቴር
የሰ. መዛግብትና ዶክመንቴሽን ቁ.2
Ethiopian Ministry of Revenues
Records & Documentation No. 2

## ዕቃ በዋስትና ስለሚለቀቅበት ሁኔታ ለመወሰን የወጣ መመሪያ ቁጥር 166/2012"

ወደ አገር ውስጥ በገቡ ዕቃዎች ላይ የጉምሩክ ስነ ስርዓት ሲፈጸም ከዕቃው የሚፈለግን ቀረጥና ታክስ መጠን ዋስትና በማስያዝ ዕቃው እንዲለቀቅ ማድረግ አስፈላጊ በመሆኑ፤

የክፍያ ጊዜ ስምምነት በጊዜ የተገደበ፤ ግልፅና ተጠያቂነት ያለበት የተመረጡ አስመጪዎች ፍትሀዊ በሆነ መንገድ የሚስተናገዱበት የአሰራር ሥርዓት እንዲኖረው ማድረግ አስፈላጊ በመሆኑ፤

ሚኒስቴሩ በጉምሩክ አዋጅ ቁጥር 859/2006 (እንደተሻሻለ) አንቀፅ 25 ንዑስ አንቀፅ (2) በተሰጠው ሥልጣን መሰረት ይህን መመሪያ አውጥቷል።

### 1. አጭር ርዕስ

ይህ መመሪያ ዕቃ በዋስትና ስለሚለቀቅበት ሁኔታ ለመወሰን የወጣ መመሪያ ቁጥር166/2012" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል።

### 2. ትርጓሜ

የቃሉ አገባብ ሌላ ትርጉም የሚያሰጠው ካልሆነ በስተቀር በዚህ መመሪያ ፡-

1/ **"ዋስትና"** ማለት አስመጪው የቀረጥና ታክስ ክፍያን በተወሰነ ጊዜ ለመክፈል ስምምነት በመግባት የሚያቀርበው የባንክ ጋራንቲ ነው።

2/ **"ቅድመ ክፍያ"** ማለት አስመጪው ላስመጣው እቃ ሊከፈል ከሚገባው ጠቅላላ የቀረጥና ታክስ መጠን ላይ በቅድሚያ የሚከፈል የገንዘብ መጠን ነው፤

3/ **"ቀሪ ክፍያ"** ማለት አስመጪው እንዲከፍል ከተጠየቀው አጠቃላይ ቀረጥና ታክስ መጠን ላይ ቅድሚ ክፍያ ከከፈለ በኃላ የሚቀረው ቀረጥና ታክስ እንዲሁም ወለድ ነው፤

4/ **"ስምምነት"** ማለት አስመጪው ወደ አገር ውስጥ ባስገባው ዕቃ ላይ ሊከፈል የሚገባውን ቀረጥና ታክስ በሙሉ ወይም በከፊል በተወሰነ ጊዜ ለመክፈል ዋስትና በማስያዝ ከኮሚሽኑ ጋር ያደረገው የክፍያ ስምምነት ነው።

በኢትዮጵያ ገቢዎች ሚኒስቴር
ቤተ መዛግብትና ዶክመንቴሽን ቁ.2
Ethiopian Ministry of Revenues
Records & Documentation No. 2

5/ "ሚኒስቴር" ወይም "ሚኒስትር" ማለት እንደ ቅደምተከተላቸው የገቢዎች ሚኒስቴር ወይም ሚኒስትር ነው፤

6/ "አዋጅ" ማለት የጉምሩክ አዋጅ ቁጥር 859/2006 (እንደተሻሻለው) ነው፡፡

7/ "ኮሚሽን" ማለት የጉምሩክ ኮሚሽን ነው፡፡

8/ ሌሎች ቃላቶችና ሐረጎች በአዋጁ የተሰጣቸውን ትርጉም ይይዛሉ፡፡

3. <u>ዋስትና በማስያዝ ዕቃ የሚለቀቅላቸው አስመጪዎች</u>

1/ በገቢ ዕቃ ላይ መከፈል የነበረበትን ቀረጥና ታክስ በተወሰነ ጊዜ ለመክፈል ዋስትና አስይዘው ዕቃ የሚለቀቅላቸው የሚከተሉት አስመጪዎች ብቻ ናቸው

ሀ) የተመረጡ የኢኮኖሚ አንቀሳቃሾች፤

ለ) የመንግሥት የልማት ድርጅቶች፣

ሐ) አምራች አስመጪዎች

መ) ሌሎች በልዩ ሁኔታ ኮሚሽኑ የሚፈቅድላቸው አስመጪዎች

2/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) የተዘረዘሩት አስመጪዎች ዕቃ ወደ አገር ውስጥ በሚያስገቡበት ጊዜ መከፈል ለሚገባው ቀረጥና ታክስ መጠን ዋስትና በማስያዝ ዕቃ የሚለቀቅላቸው ከኮሚሽኑ ጋር የክፍያ ጊዜ ስምምነት ከገቡ በኋላ ይሆናል፡፡

3/ በዚህ አንቀጽ መሰረት ለሚፈቀድ የክፍያ ጊዜ ስምምነት መቅረብ ያለበት የዋስትና ዓይነት የባንክ ጋራንቲ ብቻ ይሆናል፡፡

4. <u>ቀረጥና ታክስን በተወሰነ ጊዜ ውስጥ ለመክፈል የሚደረግ የክፍያ ጊዜ ስምምነት</u>

1/ በዚህ መመሪያ መሰረት መከፈል ለሚገባው ቀረጥና ታክስ ዋስትና በማስያዝ ዕቃ እንዲለቀቅለት የሚፈቀድለት አስመጪ የክፍያ ጊዜ ስምምነቱን በሚፈርምበት ጊዜ የቀረጥና ታክሱን 25 በመቶ በቅድሚያ መክፈል ይኖርበታል፡፡

2/ የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) ድንጋጌ እንደተጠበቀ ሆኖ በዚህ መመሪያ መሰረት ለቀረጥና ታክስ መክፈያ የሚሰጠው ጊዜ እንደሚከተለው ይሆናል፦

ሀ) ከብር 1,000,000 እስከ ብር 5,000,000 ሶስት ወር፣

ለ) ከብር 5,000,001 እስከ ብር 10,000,000 ስድስት ወር፣

ሐ) ከብር 10,000,000 በላይ ዘጠኝ ወር ይሆናል፡፡

በኢትዮጵያ ገቢዎች ሚኒስቴር
መዛግብትና ዶክመንቴሽን ቁ.2
Ethiopian Ministry of Revenues
Records & Documentation No. 2

3/ መከፈል ያለበት ቀረጥና ታክስ ከብር 1,000,000 ያነሰ ከሆነ የክፍያ ጊዜ ስምምነት አይፈቀድም

4/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (2) የተገለፀው የገንዘብ መጠን በቅድሚያ የሚከፈለውን የቀረጥና ታክስ መጠን ይጨምራል፡፡

5/ በዚህ አንቀጽ የተመለከተዉ የክፍያ ስምምነት የሚደረገዉ አስመጪዉ ከሚስተናገድበት ቅ/ጽ/ቤት የሚመለከተዉ ምክትል ስራ አስኪያጅ ጋር ይሆናል፡፡

6/ በዚህ አንቀጽ መሰረት የክፍያ ጊዜ ስምምነት የተፈቀደለት አስመጪ በንዑስ አንቀጽ (2) በተመለከተዉ ጊዜ ዉስጥ ለሚከፈለዉ ቀረጥና ታክስ ክፍያ ስምምነቱ ከተፈረመበት ቀን በፊት ባለዉ ሩብ ዓመት የንግድ ባንኮች ከፍተኛ የማበደሪያ ወለድ ምጣኔ መሰረት ተሰልቶ ወለዱ በቀሪዉ ክፍያ ዉስጥ እንዲካተት ይደረጋል፡፡

7/ በዚህ አንቀጽ መሰረት የክፍያ ጊዜ ስምምነት የተፈቀደለት አስመጪ በዉሉ በተጠቀሰዉ የክፍያ ጊዜ ያልከፈለ እንደሆነ የተያዘዉ ዋስትና ወዲያዉኑ ገቢ ይደረጋል፡፡

5. **<u>ልዩ ሁኔታ</u>**

1/ ኮሚሽነሩ ወይም ውክልና የተሰጠው ሰው እንደአስፈላጊነቱ የገንዘቡን መጠን ከግምት ውስጥ በማስገባት ተጨማሪ የክፍያ ጊዜ ሊፈቅድ ይችላል፡፡

2/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) የተመለከተው ቢኖርም በኮሚሽነሩ ውይም በተወከለው ሰው የሚፈቀደው ተጨማሪ የክፍያ ጊዜ ከሦስት ወር መብለጥ የለበትም፡፡

3/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) እና (2) መሠረት የቀረጥና ታክስ ክፍያ ጊዜ የተራዘመለት አስመጪ በተሰጠው ተጨማሪ የክፍያ ጊዜ ልክ ዋስትናውን ማራዘም አለበት፡፡

6. **<u>ያልተከፈለ ቀረጥና ታክስ ክትትል እና አሰባሰብ</u>**

1/ አስመጪው ከኮሚሽኑ ጋር ባደረገው የክፍያ ስምምነት በተገባበት ጊዜ ገደብ መሰረት እንዲከፍል ኮሚሽኑ ክትትል ያደርጋል፡፡

2/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) በስምምነቱ መሰረት ያልተከፈለ እንደሆነ ኮሚሽኑ የተያዘዉ ዋስትና ወዲያዉኑ ገቢ እንዲሆን ያደርጋል፡፡

7. **<u>ስለ ክፍያ ቀናት</u>**

1/ በክፍያ ጊዜ ስምምነት መሰረት ክፍያ የሚፈፀምበት ቀን በህዝብ በዓላት ወይም ከሥራ ቀናት ውጪ ከዋለ ክፍያው በቀጣይ የሥራ ቀን መፈፀም አለበት፤



Records & Documentation No. 2

2/ ለዚህ መመሪያ አፈፃፀም የጳጉሜ ወር የነሀሴ ወር አካል ሆኖ ይቆጠራል፤

**8. <u>የተሻሩ መመሪያዎችና ሰርኩላሮች</u>**

ይህን መመሪያ የሚቃረኑ መመሪያዎችና ሰርኩላሮች ይህ መመሪያ በሚሸፍናቸዉ ጉሰዳዮች ላይ ተፈጻሚነት አይኖራቸዉም፡፡

**9. <u>መመሪያው የሚፀናበት ጊዜ</u>**

ይህ መመሪያ በሚኒስትሩ ተፈርሞ ከወጣበት ቀን ጀምሮ ተፈፃሚ ይሆናል፡፡

አዲስ አበባ-------------------ቀን 2012 ዓ.ም

አዳነች አቤቤ

የገቢዎች ሚኒስቴር

ሚኒስትር